# <u>የክርስቶስ ትንሣኤና ሴቶች!</u>

**“በሳምንት የመጀመርያው ቀን (በኣሁን ዘመን ኣቆጣጠር እሁድ መሆኑ ነው) መግደላዊቷ ማርያም፥ ገና ጨለማ ሆኖ ሳለ፥በጧቱ ወደ መቃብሩ መጣች።ደግሞም ድንጋዩ ከመቃብሩ ኣፍ ተፈንቅሎ ኣየችው።” የዮሓንስ ወንጌል 20:1)**

የኤርትራና የኢትዮጵያ ወንድማማች ህዝቦች ለማጽናናት በዚህ አመት የጀመርነው የእግዚአብሔር ቃል ሰፊ ዝግጅት በመቀጠል፥ለዛሬም በጌታችንና መድኃኒታችን ኣስገራሚው የትንሣኤ በአል ምክንያት በማድረግ ለሁሉም ምእመናን ኣንድ ኣጠር ያለ መልእክት ይዘን ቀርበናል።

በቅድሚያ ግን ለሁላችሁ ምእመናን በተለይም **ለሴቶች እንኳን በሰላም ኣደረሳችሁ** ማለት እንወዳለን።

ከላይ ከቅድሱ ቃል ተጠቅሶ እንደምናየው የጌታችን የክርስቶስ ትንሣኤና፥አስገራሚው የሴቶች ፍቅርና ልዩ የለጋሽነት ባኅርይ ለክርስቶስ፥ሳንጠቅስ ተሻግረን ማለፍ ኣልፈለግንም።ሴቶች ልክ እንደ ምድራችን ሊመሰሉ ይችላሉ፤ከወንዶች ይልቅ በሌላ ኣካል ሊፈቀሩ ይወዳሉ።ለዚህ ነው ባሎች ለሚስቶቻቸው ያለ ማቋረጥ ሁል ጊዜ “እወድሻለሁ፥ኣፈቅርሻለሁ፥የኔ ሸጋ፥የኔ ቆንጆ ወዘተ...” ማለት ግድ የሚሆንባቸው።ከላይ ከተጠቀሰው ጽሑፍ በታች ወረድ ብለን ስናነብ፥መግደላዊቷ ማርያም እና ሌሎች በዚህ የትንሣኤ ታሪክ ስማቸው በመጀመርያ ተጠቅሶ የምናገኛቸው ሁሉም ሴቶች ብቻ መሆናቸው ነው።እንርሱ ብቻ ናቸው የክርስቶስ ፍቅር ከቀመሱ መኃላ ውለታን ለመመለስ ለህይወታቸው በጣም ኣስፈሪ በሆነበት ኣደገኛ ሰዓት ገና በጨለማና በጧቱ ሽቶ ይዘው ወደ መቃብር የመጡት፤እንጂ የሕግ ምሁራን ወይም የክህነት አገልጋዮች አልነበሩም።

ይህ ብቻ ኣይደለም፥እነ መግደላዊቷ ማርያምና ሌሎች ሴቶች የዘመኑን የኣይሁድ ባህልና ወግ ለማክበርና ሬሳውን ሽቶ ለመቀባት በሶስተኛው ቀን ወደ መቃብሩ በመምጣታቸው፥ኣንድ ነገር በሰአቱና በፕሮግራሙ መከናወን እንዳለበት ኣምነው ወድያው የማድረግ ባኅሪያቸውና ጥሩ ጎድናቸውን ያሳይያል።ለመሆኑ የትንሣኤ ብሥራት ከመልኣክቶች ተቀብለው ለኃዋርያቶችና ለሌላ ሁሉም ህዝብ በመጀመርያ ደረጃ ያደረሱትስ እነርሱ ኣይደሉምን፧

ታድያ ለምንድነው ቤተ ክርስትያንም ትሁን ሌሎች ሰዎች፥ይህንን ትልቅ የሴቶች ሚስጥርና ኃይለኛ ጎድናቸውን ሳይጠቅሱ የሴቶች ደካማነትና ሰነፍነት ብቻ ሲያወሩ የኖሩት፧ትልቁን የክርስቶስን የትንሣኤ ብሥራት ለሌሎች ያደረሱት ሴቶች፤በኣሁኑ ሰአትስ በቤተ ክርስትያን በመድረክ ቁመው የክርስቶስ ፍቅርና የትንሣኤ መልእክት ለምእመናን ቢያደርሱና የራሳቸውን ልምምድ ለሌላ ቢያካፍሉ ምን ኣለበት፧

ስለዚህ ኣስተሳሰባችንና አመለካከታችን ቀይረን፥በአፈታሪክ የሚነገረውን ተረትና ምሳሌ ትተን ከመጽሓፍ ቅዱስ ጋር ዛሬ ከተስማማን፥እነዚህ ወንድማማች የሆኑት የኤርትራና ኢትዮጵያ ህዝቦች በሞላ ከድህነት በተሎ ተላቅቀውና ራሳቸውን ችለው ካደጉት ኣገራት ጋራ እንደሚጠጉ ጥርጥር የለንም።

በድጋሚ እንኳን አደረሳችሁ!

ቸር ይግጠመን!!!

ድያቆን ኢያሱ (ኦባማ)

(Please visit our family’s website on <u>http://www.ozovoh.org/</u> or contact ozjsfamily@gmail.com